ቨርቹወል የትምህርት ክፍል ሪኮርድ ስለማድረግ፣ ስለ ተማሪ ብትህውነት እና ደህንነት የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የወላጅ መመሪያ

በቀጥታ የሚተላለፍ ቨርቹወል ትምህርት መስጠት የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አስፈላጊ የማገገሚያ እቅድ አካል ነው። የቀጥታ ስርጭት ቨርቹወል ትምህርት ማየት ለማይችሉ ቤተሰቦች እና ተማሪዎች፣ በቀጥታ የተሰጠው ቨርቹወል ትምህርት በቪድኦ እና በድምፅ ሪኮርድ ይደረጋል። ሪኮርድ የተደረገው ትምህርት በቀጥታ ስርጭት የቀረበውን የትምህርት ይዘት ማየት-ለሚፈልጉ እንደ ሪሶርስ ያገለግላል። በርህራሄ፣ እንደሁኔታ ማመቻቸት፣ በተባበረ ትጋት እና የተማሪ ገመና እና ደህንነትን ስለ መጠበቅ ያለውን መመሪያ በማስተዋል በጥንቃቄ ሪኮርድ ማድረግ ተግባራዊ እንዲደረግ ያስችላል። ተማሪዎች ሪኮርድ የተደረጉትን የክፍል ትምህርቶች እስከ 72 ሠዓት በ "myMCPS class" ለማግኘት ይችላሉ።

አጭር የቪድኦ ዙም ሪኮርድ የተደረገ ምልከታ

ትምህርት የሚሰጥበት ዙም ቪድኦ ኮንፈረንስ በመጠቀም ሪኮርድ ይደረጋል። ግላዊ ገመናን እና ደህንነትን በትክክል በመጠበቅ ከስፐሪንግ ጀምሮ ዙም ቪድኦ ኮንፈረንስ በሥራ ላይ እንዲውል አድርገናል። እስካሁን ድረስ፣ ተማሪዎች በካሜራ ሲታዩ፣ ስማቸው እና ምስላቸው ለአስተማሪ እና ለሌሎች ተሳታፊ ተማሪዎች ይታያል። ቢሆንም፣ በቀጥታ ስርጭት በሚተላለፍ ትምህርት ወቅት የተማሪዎች ስም አይታይም እና ምስላቸውንም በተቻለ መጠን በካሜራው ላይ ለማሳነስ ጥረት ይደረጋል። ከእርስዎ ልጅ የሚቀርቡ ጥያቄዎች እና አስተያየቶችም እንደዚሁ ሪኮርድ ይደረጋሉ። በዚህ ያልታሰበ ወረርሽኝ ወቅት እንደሁኔታው የማመቻቸት flexibility አስፈላጊነት እና ስለ ተማሪ ግላዊ ገመና የተቻለውን ሁሉ ጥንቃቄ የምናደርግ ይሆናል።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ቨርቹወል የሚሰጡ ትምህርቶችን ሪኮርድ ስለማድረግ በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎችን የዚህ አዲስ የትምህርት አሰጣጥ ሁኔታ ግንዛቤ እንዲኖራችሁ እና ለልጆቻችሁ የሚሻለውን እንድትወስኑ በዚህ ዶኩመንት ላይ አጠናቅረናል። የእኛን የቨርቹወል ትምህርት ሁኔታ ይበልጥ እየተገነዘብን፣ እያጠራን እና እያሻሻልን ስንቀጥል በዚህ ዶኩመንት ላይ ያለው መመሪያ ለውጥ ሊደረግበት ይችላል። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የልጆቻችሁን ገመና ለመጠበቅ ትርጉም ያለው እርምጃ ሁሉ እንደሚወሰድ እና MCPS ሌሎች ሃላፊነት ያልተሰጠውን እርምጃ እንደማይወስድ እባክዎ ይገንዘቡ። የሆነ ሆኖ፣ ይህ መመሪያ ተግባራዊ የማይሆን ከሆነ በፍጥነት ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ ቁርጠኞች መሆናችንን እናረጋግጥልዎታለን። እነዚህ ደምቦች ተጥሰዋል ብለው ካመኑ እባክዎ ለእርስዎ ልጅ አስተማሪ ወይም አስተዳዳሪ ያሳውቁ። በዚህ ሁላችንም አብረን ነን።

አፈጻጸም እና አቀራረብ

ዋናው ግብ ከአስተማሪ በቀጥታ የሚሰጠውን ትምህርት-እውቀት (ለተማሪዎች ከሚደረገው በተለየ) ለቤተሰቦች ለማስጨበጥ ነው። በዚህ ረገድ፣ ሪኮርድ ለማድረግ የሚከተለውን አሠራር ተግባራዊ አድርገናል፦

- "Zoom chats" አስተማሪ chat feature ከከፈተ(ች) በኋላ ተማሪዎች ከአስተማሪ ጋር በውይይት እንዲሣተፉ ያደርጋል።
- በ "Zoom" ላይ የሚገኘው መቅረጫ አጠቃላይ የትምህርት ክፍል ውይይት ከሚቀርጽ በስተቀር ከአስተማሪ ጋር የሚደረጉ ግላዊ ንግግሮችን-ውይይቶችን አይቀርጽም። ከዚህ ሌላ በመግሪያ ክፍል ሪኮርድ ላይ የተማሪ ስም አይገለጽም።
- ለአስተማሪዎች ምን እና ማን ሪኮርድ እንደተደረገ በመለየት ለመቀነስ የሚያስችል አማራጭ ዘዴዎችን ለይተናል። ግቡ በአስተማሪ እና በቀጥታ በሚተላለፈው የትምህርት ሞዴል ላይ ትኩረት እንዲደረግ ነው። እያንዳንዱ አስተማሪ ከዚህ በታች ካሉት አማራጮች ውስጥ ለተማሪዎቹ እና ለቤተሰቦቻቸው የሚመቸውን አቀራረብ ይመርጣል-ትመርጣለች።
    - <u>የመጀመሪያው ተመራጭ ዘዴ</u> : ሪኮርድ የሚደረገው ከአስተማሪ ለክፍል ተማሪዎች በቀጥታ የሚተላለፍ ትምህርትን ሲሆን ካለቀ በኋላ ከተማሪዎች ጋር ምንም አይነት ግንኙነት ከመጀመሩ በፊት ሪኮርድ ማድረግ ይቆማል።
    - <u>ሁለተኛው ተመራጭ ዘዴ</u> : ከክፍል ውጪ ትምህርቱን በቅድሚያ ሪኮርድ ማድረግ (የትምህርቱን ዋና ይዘት እና ሞዴል)። አስተማሪ ሪኮርድ ሳይደረግ በቀጥታ ትምህርት ይሰጣል-ትሰጣለች፣ እና በአስተማሪ የተሰጠውን ትምህርት ለመገንዘብ ከቀጥታ ስርጭት ውጪ የተቀረጸው የትምህርት ቪድኦ ይለቀቃል። በሁለተኛ ደረጃ፣ አስተማሪ በተመሣሣይ ደረጃ ከሌላ ሰክሽን-ክፍል ሪኮርድ የተደረገ ትምህርት በአስተማሪ ሊቀርብ ይችላል ሪኮርድ የማድረጉን ጥራት በሚነካ ደረጃ ተማሪዎች ያልመረጡት ካልሆነ በስተቀር። ይህኛው ዘዴ ሊታሰብ የሚችለው ትምህርቱ ሪኮርድ የተደረገበትን ጥራት ስላልወደዱት በርካታ ተማሪዎች ያልፈለጉ ከሆነ ሪኮርድ የተደረገው እና ትምህርቱ ያለበቂ የተማሪዎች ተሳትፎ የሚቀር ከሆነ ነው።
    - <u>ሦስተኛው ተመራጭ ዘዴ</u> : ትምህርት በቀጥታ እየተሰጠ ትምህርቱን እና ተማሪዎችን ሪኮርድ ማድረግ

ትምህርቱ ሪኮርድ እየተደረገ መሆኑን እንዴት ለማወቅ እንችላለን?

- ቨርቹወል የቀጥታ ስርጭት ትምህርት የሚጀመረው የተማሪዎች ማይክሮፎን እና ቪድኦ ካሜራዎች በጠቅላላ ድምፅ እንዳይሰጡ ተደርገው ወይም ዝግ ተደርጎ ነው።
- እያንዳንዱ ትምህርት በሚጀመርበት ሠዓት ከተማሪዎች ስለሚጠበቅ ስነምግባር በመግቢያው ላይ ስላይድ ወይም አጭር መግለጫ ይሰጣል።
- አስተማሪዎች መቼ ሪኮርድ ማድረግ እንደሚጀምሩ እና መቼ እንደሚጠናቀቅ ለተማሪዎች ይገልጻሉ።
- ትምህርቱ በሚጀመርበት ሠዓት፣ ትምህርቱ-ክፍሉ ሪኮርድ እየተደረገ መሆኑን የሚገልጽ ማስታወቂያ ሁሉም ተማሪዎች ይመለከታሉ።

ሪኮርድ የተደረገው የት እንደሚቀመጥ እና ተደራሽነት ያለውስ ማነው?

- አስተማሪዎች ትምህርቶቹን በ "myMCPS classroom" ላይ ይለጥፋሉ። ተማሪዎች ቪድኦ ለማግኘት የሚችሉት በ MCPS የኢሜይል አካውንታቸው ብቻ እንዲሆን የተወሰነ ነው። የመማሪያ ክፍሉ ተደራሽነት የሚኖራቸው የክፍል ተማሪዎች ብቻ ናቸው።
- ተማሪዎች እና ቤተሰቦቻቸው ቪድኦውን ለመጫን አይችሉም። ተማሪዎች እና ቤተሰቦች ቪድኦዎችን ወደ ኮምፒውተሮቻቸው፣ clouds፣ እና ወዘተ መጫን እንደማይችሉ ዘግተነዋል።

የተማሪን ገመና ለመጠበቅ ምን ተጨማሪ መከላከያ ተደርጓል?

- በመደበኛ ክፍል የ MCPS ሠራተኞች የተማሪን ማንነት የሚገልጽ መረጃ (PII) ይፋ እንደማያደርጉ ሁሉ፣ [1]ይህ መስፈርት ኦንላይን ትምህርት በሚሰጥበት ወቅትም ይተገበራል።
- ትምህርቶቹ ሪኮርድ የሚደረጉት ለትምህርታዊ ዓላማ ብቻ ነው። የተማሪን ገመና ከመጠበቅ አኳያ በተማሪ አማካይነት የሚቀርቡ አከራካሪ የሆኑ አርእስቶች (በሌሎች ተማሪዎች ወላጆች፣ ቤተሰቦች፣ የሚታይ ወይም ከተማሪ ጤንነት ጋር የተገናኙ ጉዳዮች) ምክንያት በርካታ አስፈላጊ ጥንቃቄ መደረግ ያለባቸው ሪኮርድ የማድረግ መስፈርቶች ይኖራሉ።
  - ሪኮርድ ለማድረግ ተመራጭ የሆነው ዘዴ አስተማሪ በቀጥታ ስርጭት የሚያቀርበውን-የምታቀርበውን ወይም ሲያስተምር-ስታስተምር እና ከተማሪዎች ጋር ውይይት ሳይጀመር በፊት መቅዳት-ሪኮርድ ማድረጉን ማቋረጥ ነው።
  - ሌላኛው ተመራጭ ዘዴ ከትምህርት ክፍል ድባብ ውጪ በሆነ ጊዜ (ዋናውን የትምህርት ክፍል እና ሞዴል) ትምህርቱን ሪኮርድ ማድረግ ይሆናል። ለእነዚህ ሁለቱም ዘዴዎች፣ አስተማሪዎች የቅጂ መብትን ስለማክበር ህግ (copyright law) መጠበቅ እንዳለበት ማስታወስ አለባቸው።
  - ከተማሪ ጋር ንግግር-ውይይት እየተደረገ ሪኮርድ የሚደረግ ከሆነ፣ አንዳንድ ጥንቃቄዎች ይደረጋሉ።
- በጠቅላላ አስተማሪዎች እና የ MCPS ሠራተኞች ከዚህ በታች የተገለጹትን ጥንቃቄዎች ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

- ብቁ ተማሪዎች እና ወላጆች/ሞግዚቶች ቨርቹወል ትምህርት በሚሰጥበት ወቅት ተማሪው(ዋ) ሪኮርድ እንዲደረግ እንደማይፈልግ-እንደማትፈልግ ParentVUE በመጠቀም በ MCPS Form 281-13 ቅጽ ላይ መግለጽ ይችላሉ አመታዊ የመረጃ መግለጫ እና የተማሪ ገመና-Annual Notice for Directory Information and Student Privacy..የሚለውን ምልክት በመምረጥ፡- ካልፈለጉ ይህንን ምልክት ለመምረጥ ይችላሉ፡- “Do not include my student’s image and voice in the recording of virtual lessons for future viewing by students in the same class.” MCPS Form 281-13 ዓመታዊ የመረጃ መግለጫ እና የተማሪ ገመና ቅጽ - Annual Notice for Directory Information and Student Privacyበተጨማሪ ከ MCPS በይነመረብ ላይ ወይም ከተማሪው(ዋ) ትምህርት ቤት ለማግኘት ይቻላል። ከበርካታ ተማሪዎች/ወላጆች የተገኘው ሪፖርት በቨርቹወል የትምህርት ክፍለጊዜ ሪኮርድ ለመደረግ የማይፈልጉ ተማሪዎችን እንዲለዩ ለአስተማሪዎች ይሰጣል።

- ከእያንዳንዱ ሪኮርድ የተደረገ ትምህርት ክፍለጊዜ መጀመሪያ ላይ ተማሪዎች ሪኮርድ እየተደረጉ መሆናቸውን አስተማሪዎች ለተማሪዎቹ መግለጽ ይኖርባቸዋል፣ እና እንደማይፈልጉ ገልጸው ከሆነ፣ አስተማሪው(ዋ) ካሜራውን እና/ወይም ተማሪው(ዋ) ክፍት አድርገው ከሆነ ማይክሮፎኑን እንዲዘጋ ያደርጋሉ።
- ሪኮርድ የሚደረገው ለትምህርታዊ ዓላማ ብቻ ነው። ኃይማኖታዊ ወይም ባህላዊ ሥርዓት ወይም ልማድን የመሣሰለ ጥንቃቄ ይዘት ያላቸው ሪኮርድ መደረግ የለበትም። ቀላል አጭር ፈተናዎች እና የባህርይ ተፅእኖን መመርመር የመሣሠሉት ሪኮርድ አይደረጉም። እንደዚህ አይነት ይዘት ያላቸው በስህተት ሪኮርድ ተደርጎ ከሆነ፣ በፕላትፎርሙ ላይ ከመቅረቡ በፊት መሠረዝ አለበት።
- ሪኮርድ የተደረጉ ትምህርቶች ከመሠረዛቸው በፊት 72 ሠዓት ስለሚቆይ ለማግኘት ይቻላል፣ ከዚያ በኋላ በቀጥታ ከዙም መድረክ - Zoom platform ላይ ይሠረዛል-ይጠፋል። ነገር ግን፣ ትምህርት እየተሰጠ ባለበት ጊዜ ተማሪን ዲስፕሊን የማድረግ ሁኔታ ከተከሰተ፣ ሪኮርድ የተደረገው በአስተማሪ አማካይነት ለትምህርት ቤት ርእሰመምህር/ተወካይ ይሰጣል። ሪኮርድ ሲደረግ የሠራተኛ መጥፎ ስነምግባር ሪኮርድ ተደርጎ ከሆነ፣ ወይም የተማሪ፣ የሠራተኛ ወይም የወላጅ ስጋት የሚሆን ነገርን ያካተተ መሆኑን ሠራተኛ ከተገነዘበ፣ ተመሣሣይ ደምብ ይተገበራል።

ሪኮርድ የተደረገው **72** ሠዓት እንዲቆይ የሚደረገው ለምንድነው?

- 72 ሠዓት እንዲቆይ ጊዜያዊ ገደብ የተደረገበት ምክንያት የቪድኦ ተደራሽነቱ ገመናን ለመጠበቅ ተጨማሪ በመሆኑ ነው። ሪኮርድ የተደረጉ የቪድኦ ትምህርቶች በሙሉ በእኔ "myMCPS classrooms" ላይ ለረዥም ጊዜ እንዲቆይ መተው የቪድኦ ተደራሽነትን ጊዜ ያራዝማል።
- ይህ ውስንነት ሁሉም ክፍሎች ሪኮርድ እንዲደረጉ ያስችላል። myMCPS classroom የማቆያ ውስንነት አለው። ትምህርቶቹ የሚቆዩበት ሠዓት ካልተገደበ፣ መረጃውን የማቆያ ቦታ እና ሁሉን ክፍሎች ሪኮርድ የማድረግን አቅም ይቀንሳል ማለት ነው።

---

[1] ማንነትን የሚገልጹ መረጃዎች፣ ወይም በ PII በከፊል እንደተገለጸው፣ የተማሪ ወላጆች ወይም ሌላ የቤተሰብ አባላት ስም እና አድራሻ፣ ማንኛውም ሌላ ማንነትን የሚገልጹ (ለምሳሌ፡- የሶሻል ሰኩሪቲ ቁጥር፣ ወይም የተማሪ መታወቂያ ቁጥር)፣ በተዘዋዋሪ ገላጭ የሆኑ (ለምሣሌ፡- የተማሪ ልደት ቀን ወይም የትውልድ ቦታ፣ የተማሪ ወላጅ እናት የመጀመሪያ ስም)፣ ወይም ሌላ በተናጠል ወይም በጣምራ ስለሁኔታዎቹ እውቀት ያልነበረው ሰው/ስለሁኔታዎቹ እውቀት ያልነበረው ሰው/የትምህርት ቤት ማህበረሰብ ዘንድ የተማሪን ማንነት በእርግጠኝነት እንዲታወቅ የሚያደርግ ማለት ነው። PII ስለ ተማሪው(ዋ) ወይም ስለተቤተሰብ፣ ጥንቃቄ የሚሻ የጤንነት መረጃ ወይም ከተማሪ የትምህርት ሪኮርድ የተገኘ ማንኛውንም መረጃ የሚያካትት ይሆናል።

- በፈቃድ የሚቀሩ ተማሪዎች ሪኮርድ የተደረጉ የክፍል ትምህርቶችን ለመጠቀም ከፈለጉ፣ ለማመቻቸት አስተማሪ ማነጋገር ይኖርባቸዋል።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሪኮርድ እንዳይደረጉ የመረጡትን ተማሪዎች እንዴት ያስተናግዳል?

- ሪኮርድ መደረግ የማይፈልጉ ተማሪዎች ካሜራቸውን እና የድምፅ መቅረጫውን የመዝጋት ሃላፊነት አለባቸው።
- ሪኮርድ መደረግ ለማይፈልጉ ተማሪዎች፣ አስተማሪ በሚጀምርበት ሠዓት ካሜራ እና/ወይም የተማሪው(ዋ)ን ማይክሮፎን ይዘጋል-ትዘጋለች።
- ምክንያቱም አንዳንድ ተማሪዎች ሪኮርድ መደረግ አይፈልጉም እና ውይይትም ላይ ለመሣተፍ አይፈልጉ ይሆናል (ወይም ማድረጉን አይችሉ ይሆናል)፣ ስለዚህ ት/ቤት ሌላ በትምህርት ለመሣተፍ የምትችሉበትን ሌላ ብልሃት ለማግኘት ከእናንተ ጋር ይሠራል። ሪኮርድ መደረግ የማይፈልግ-የማትፈልግ ተማሪ በሌላ አማራጭ ዘዴ ለመሣተፍ እስከቻለ(ች) ድረስ በውሣኔው(ዋ) ምክንያት መጎዳት አይኖርበ(ባ)ትም።
- አስተማሪዎች እያንዳንዱን ጉዳይ በሚመለከት በርካታ ተማሪዎች ሪኮርድ እንዳይደረጉ የመረጡ ከሆነ ሙሉውን የተማሪ ተሳትፎ-ግንኙነት ሪኮርድ ይደረግ  እንደሆነ ለመወሰን ከአስተዳዳሪዎቻቸው ጋር ይሠራሉ። ለምሳሌ፡- በርካታ ተማሪዎች ሪኮርድ እንደማይደረጉ መርጠው ከሆነ፣ እና ሪኮርድ የተደረገው ትምህርት እና የማስተማር ጥራት የተማሪዎች ተሳትፎ የጎደለው መሆኑን አስተማሪ ከወሰነ(ች)፣ ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ሁለተኛውን ተመራጭ ዘዴ ይሄውም ተማሪዎች በሌሉበት ሪኮርድ ማድረግን መምረጥ ይችላል-ትችላለች።

ተማሪዎች ሪኮርድ ለመደረግ ካልፈለጉ ቅጣት ይኖራል?

- አንዳንድ ተማሪዎች ካሜራቸውን ከፍተው ሪኮርድ ሲደረጉ ምቾት እንደማይሰማቸው የ MCPS ሠራተኞች ይገነዘባሉ። የቪድኦ አሠራርን መጠቀም ለተማሪዎች ግዴታ አይደለም። ወላጆች/ሞግዚቶች የቪድኦ አሠራርን በማናቸውም ጊዜ ወይም በልዩ ሁኔታ ላይፈልጉ ይችላሉ።

ተማሪ ተገቢ ባልሆነ ስነምግባር ከተጠመደ(ች) ምን ይሆናል?

- አግባብነት የሌለው የሚጠረጠር ስነምግባር በጠቅላላ በ [በተማሪ የስነምግባር ደምብ-መመሪያ መሠረት ይመረመራል።]
- በትምህርት ረገድ እምነት የጎደለው ስነምግባር፣ ማስፈራራት/ማስጨነቅ/ዛቻ፣ ወይም ቴክኖሎጂን አግባብ ባልሆነ መንገድ መጠቀም ተገቢ እርምጃ ይወሰዳል። የዲስፕሊን እርምጃዎቹ ከማስጠንቀቂያ እና ከወላጅ ኮንፈረንስ እስከ ማስወገድ እና ከትምህርት እስከማባረር ወይም በኦንላይን ትምህርት ሲሰጥ ካሜራ እና የድምፅ መቅረጫ ማስወገድ ድረስ እርምጃ ሊያስወስድ ይችላል።

የእኔ ልጅ በቪድኦ ሪኮርድ እንዳይደረግ-ሪኮርድ እንዳትደረግ ከመረጥኩ፣ ሪኮርድ እንደማይደረግ አስተማሪዎች እንዴት ማወቅ ይችላሉ?

- ከተሰባሰቡት መረጃዎች በተጨማሪ፣ ምርጫቸው ግልጽ መሆኑን ቤተሰቦች አስተማሪን እንዲያስጠነቅቁ እንጠይቃለን።
- ቤተሰቦች ትምህርት ቤትን በማነጋገር ምርጫቸውን ለመቀየር ይችላሉ። ትምህርት ቤት ያለመፈለግ ምርጫቸውን የማሳወቅ ሃላፊነት አለበት።

**PII** ያለው ቪድኦ ማጋራት የሚያስከትለው እርምጃ አለ?

- ቪድኦው እነዚህን ድንጋጌዎች በመጣስ ሪኮርድ ተደርጎ ለሌሎች ያጋሩት ከሆነ፣ ተማሪዎች የዲስፕሊን እና/ወይም የእርምት እርምጃ፣ ሊወሰድባቸው ይችላል። ሪኮርድ የተደረጉ ትምህርቶችን የማግኘት ጥቅም እስከማጣት ድረስ፣ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ፣ እና የዲስፕሊን እርምጃዎችን ያስወስዳል።
- ያለአግባብ ቪድኦ ለሌሎች ተላልፎ ከሆነ፣ ለርእሰመምህር ያሳውቁ። ተገቢ እርምጃ ስለመውሰድ የእርስዎ ርእሰመምህር ከዋና ጽ/ቤት ጋር ይሠራል።
- የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) እነዚህን ደምቦች እና ጥንቃቄዎችን ለማስፈጸም ቁርጠኛ ነው።